# አሥራት አትረሳም

ፕሮፌሰር አስራት ሞተ ብለው
አረዱኝ ከእንቅልፌ ቀሰቅሰው።
መቼ አስራት እንደሰው ይሞታል
ከኢትዮጵያ ጋር ለዘለዓለም ይኖራል።

አሥትራ ወገኑን ሲያክም በወጣትነቱ
እናቱ ታመመች ሲደክም ጉልበቱ።

እንዲህ ነው ሰው መውደድ፡
እንዲህ ነው ፍቅር፤
ሕይወን ሰውቶ ለማዳን መጣር።

አሥራት ሲባል ይመስለኝ ነበር
የቤተ ክርስቲያን መባ እና ግብር፤
ለካስ አሥራት ቅዱስ መሰዋእትም ይሆናል
ሥርአቱ በኢትዮጵያኖች ዘንድ ተጀምሮአል።

ሁሉም ይሞታል አፈርም ይሆናል
የከፈለ አሥራቱን ከሙታን ይነሳል።

የግብር አሥራትን ካች አምና ከፍለን
ለምን እንላለን በዕዳ ተያዝን።

ትንሹም ትልቁም ነፍሱን ያከብራታል
አሥራት ግን ንቄታል ይገርማል ይደንቃል
የቴዎድሮስን ፈለግ ፈሩን ተከትሏል።

በስጋ እናታችን ጡት ባጠባችን
አምጸን ወይነን አጉል ታብየን
አሥራቷንም ነጥቀን ተካፍለን በልተን
እግዚአብሄር ተቆጥቶ ይኸው በተነን።

ምንም ቢጠቈቁር ቢገረጣ ገጹ
አሥራት እንዲህ አለ በሰለለ ድምጹ፤
"ዋስ ጠበቃም የለሽ ብቻሽን ቀርተሻል
ልጆችሽ ከሰዉ ሽ እጅግ ታውከሻል
እምዬ ኢትዮጵያ እጆችሽን ዘርዚ
ከቸሩ እግዚአብሄር መፍትሄ ፈልጊ።"

አሥራት ወልደየስ የሀገሩን ብሶት
ለሰዎች ተናግሮ አንሰማህ ቢሉት
ተጉዞ ነጎድ ወደ እግዜር ችሎት
ቅን ፈራጅ ለሆነው አቤት ለማለት።

ሕዝባችንን ልቀቅ ከተሰኘው የግጥም መደብል የተወሰደ
ደራሲ አስፋወሰን ዓለምሰገድ
የታተመው September 2005
ethioasfawosen@yahoo.com